ትምህርት 13

## ስለ ጸሎት ክፍል 2

*እግዚአብሔር ጸሎታችን እንዲመለስ ይፈልጋል/ፈቃዱ ነው፡- ማቴ 7፡7-8፣ 8፡2-3፣ ዮሐ 10፡10፣16፡23-24፣*

*የጸለዩበት ጉዳይ መልስ ማግኘት ጸልየው ካገኙት ነገር ባሻገር ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን፣ በእርሱ ያለ መተማመንን፣ ለእርሱ ፈቃድ የመኖር ደረጃን ቀድሞ ከነበረበት ከፍ ያደርጋል፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች እየጸለዩ መልስ አለማግኘት ግን በእርሱ መታመንን፣ ለፈቃዱ የመኖር ህይወትን፣.. ይጎዳል፡፡ ጸሎት መጸለይን አድካሚና የግዴታ ስራ ዓይነት ያደርገዋል፡፡ በክርስትና ሕይወት ሁሉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያደርጋል፡ ስለዚህ ጸሎት መልስ እንዲያገኝ የአማኝ ሕይወት እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ዝግጁ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ ወደዚያ ዝግጅት ካልደረሱ ሳይጸልዩ መቆየት/መተው ሳይሆን እየጸለዩ ዝግጅቱን አብሮ ማካሄድ ነው፡፡*

**የጸሎት ቅደም ተከተል፡-**

*ሀ. ራስን መርምሮ ንስሃ መግባት ለ. እግዚአብሔርን ማመስገን*

*ሐ. እግዚአብሔርን ማወደስ መ. ሊጸለይበት የተፈለገው ጉዳይ (የጸሎት አርዕስት) ማስከተልና በመጨረሻ ጸሎት ማብቂያ ላይም አግዚአብሔርን ማመስገን፤*

**ለጸሎት ተሰሚነት የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎች፡፡**

1. *ወደ ተከበረ ሰው ፊት ከመቅረብ በፊት ምንም ጉድፍ እንዳይገኝበት ልብስና ሰውነትን በማጽዳት እንደሚጀመር፣ ወደ ሌሎች የጸሎት አርዕሰት ከመግባት በፊት* ***ራስን በእግዚአብሔር ቃል እይታ በመመርመር ንስሃ መግባት*** *ያስፈልጋል፡፡ ኃጢአት በማድረግ ጸንቶ መቀጠል እግዚአብሔር የሚጸልዩት ጸሎት እንዳይሰማ ምን ያህል አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያደርግ የሚያሳዩት በርካታ ጥቅሶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-*
   *ሰቆ ሔር 3፡40፡ "መንገዳችንን እንመርምር፤ እንፈትን፤ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ።" ሳይናዘዙትና ንስሃ ገብተው ሳያስወግዱት የቆየ ኃጢአት ካለ ራስን መርምሮ መናዘዝና ንስሃ መግባት ማስወገድ፡፡ (2ቆሮ 13፡5፤)*
   ምሳ 28፥13፣ "ኀጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝና የሚተወው ግን ምሕረትን ያገኛል።"
   ምሳ 28፥9፣ "ሕግን ላለመስማት ጆሮውን የሚደፍን፣ ጸሎቱ እንኳ አስጸያፊ ነው።"

   *ኃጢአት እንደሰሩ የሚታወቅ ነገር ሳይኖር በልበ ሙሉነት/በድፍረት ወደ ፈጣሪ ለጸሎት መቅረብ እንዲቻል ያልተናዘዙትና ንስሃ ገብተው ያላስወገዱት የቆየ ኃጢአት ካለ ራስን መርምሮ በማግኘት መናዘዝና ንስሃ በመግባት ያንን ኃጢአት ማስወገድ/መተው ነው፡፡ መዝ 66፡18፡፡* ***ሀ.*** *የበደሉት ሰው ካለ አስቀድሞ ከዚያ ሰው ጋር ተነጋግሮ ቅሬታን መፍታት፣ ማቴ 5፡23-24፡፡* ***ለ.*** *በሰው የተበደሉት ነገር ካለም ሌሎችን ይቅር የሚል ይቅር ይባላልና የበደለ ሰው ካለም ይቅር በማለት ከቂመኝነት መውጣት፡፡ ማር 11፡24-26 ፡፡ ከሰው ሁሉ ማለትም ከማያምኑት ጋር ጭምር በሰላም ለመኖር ጥረት ማድረግ፡፡* ***ሐ.*** *የራስን ስህተት ሳያስተካክሉ ሌላውን ሰው የተቹበት/የኮነኑበት ጉዳይ ካለና ማንኛውም ህሊናን የሚወቅስ/ የሚታወቅ ኃጢአት ካለ ራስን መርምሮ ኃጢአት ሆኖ በተገኘው ነገር ተናዝዞ ንስሀ መግባት፣ ሉቃ 6፡37፣* ***መ.*** *በቀጥታ እግዚአብሔር ራሱን ያሳዘኑበት ጉዳይ ካለም ይቅርታ ጠይቆ ይቅር እንደተባሉ በማመን ያንን የህሊና ወቀሳ ከማስተናገድ ሙሉ በሙሉ መውጣት በልበ ሙሉነት አምላካችን ፊት መቅረብ፡፡ ዕብ 10፡19፡ በእግዚአብሔር ፊት ንስሃ ከገቡ በኋላ መልሶ ያንኑ ኃጢአት ከመደጋገምም መቆጠብ፡፡ 1ዮሐ 1፡6-7 (ኢሳ 58፡1-14፣ 59፡1-2፤ መዝ 81፡13-14፣ ኤር 5፡22-25)*

2. **በዚህ ሁኔታ ንስሃ ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር በመራራት ምህረት ስላደረገና ታላቅ ውለታውን በማነሳሳት ወደ እርሱ የሚቀርበው ጸሎትም ሁሉ እንደሚሰማ በማመን ማመስገን ያሻል፡፡**

3. ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ፊት ለመቅረብ ወደር የሌለው ታላቅ ባሕርያቱና በብርቱ ክንዱ ያከናወናቸው አስደናቂ ስራዎቹን በማነሳሳት ማሞገስ /ማወደስ/ ክብር መስጠት ይገባል፡፡

   በእርሱ የሚያስመካ፣ እንዲፈራና እንዲከበር የሚያደርጉት ባህርያቱንና ታላላቅ ተግባራቱን በማነሳሳት ታላቅነቱን በቃል መናገር ወይም መዘመር ተገቢ ነው፡፡ ፊሊጵ 4፡6፤ ዕብ 13፡15፣ እግዚአብሔር መወደስና መመስገን ያለበት ሁኔታዎች ስለተመቻቹ ሳይሆን ስለተገባውና ስለማይለዋወጥ ነው፡፡

4. **እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሕይወት መገኘት** (ቢ ኢን ራይት ሪሌሽንሺፕ ዊዝ ጋድ፤) ማቴ12፡50
   እግዚአብሔርን መታዘዝ የጸሎት መልስ ለማግኘት ወሳኝ ነገር መሆኑን የሚያሳዩ የቃሉ ክፍሎች፡ -
   **ምሳሌ 15፥8** "እግዚአብሔር የክፉዎችን መሥዋዕት ይጸየፋል፤ የቅኖች ጸሎት ግን ደስ ያሰኘዋል።"
   **መዝ 34፥15** "የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ ጻድቃን ናቸው፤ ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ክፍት ናቸው።"
   **ሉቃስ 6፥46** "እኔ የምለውን አታደርጉም፤ ታዲያ ለምን፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ' ትሉኛላችሁ?"
   **ዕብ 12፥14**፣ "ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚቻላችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ለመቀደስም ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት አይችልም፤"
   **1 ሳሙ15፥22**፣ "ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ "ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር፣ በሚቃጠል ቍርባንና መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ! መታዘዝ ከመሥዋዕት፣ ማዳመጥም ከአውራ በግ ሥብ ይበልጣል።"
   **1 ዮሐ 3፡21-22** ወዳጆች ሆይ፤ ልባችን የማይፈርድብን ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረት አለን፤
   22 ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና በፊቱም ደስ የሚያሰኘውን ስለምናደርግ የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እንቀበላለን። (ኢሳ1፡10-15)
   **ሚክ 6፥8** "ሰው ሆይ፤ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል፤ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? ፍትሕን ታደርግ ዘንድ፣ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፣ በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን?"

   **የመታዘዝ ሕይወት በሁለት ክፍለን ማየት ይቻላል።**
   **ሀ/ ከእግዚብሔር ከራሱ ጋር በሚኖር ሕብረት**፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያማረ ሕብረት/ተዛምዶ ሊኖር ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔርን ያልታዘዙት ነገር ካለ በመጸጸት ንስሃ ገብቶ ከዚህ በኋላ ባለው ጊዜ ለመታዘዝ ከልብ ወስኖ መቀጠል ነው፡፡ በሰሩት ኃጢአት ተጸጽተው ንስሃ ከገቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ ከኃጢአት እየራቁ መሄድ ከቀጠሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት ያማረ ይሆናል፡፡ ከእርሱ ጋር ያለ ኅብረት ሁልጊዜ የተጠበቀ ከሆነ እርሱም ሁልጊዜ በባሮቹ ደስ ይሰኛል፡፡ ዮሐ 15፡10፣ 14፣ 15፡7-8 እነዚህ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ያስተማረውን ቃል ሁሉ በመታዘዝ መተግበርን ያመለክተሉ፡፡
   እዚህ ላይ ልብ ሊሉት የሚገባው፣ በታዛዥ ልጅና በፍጹም ጻድቅ ሰው መካከል ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ እግዚአብሔርን እየታዘዙት ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈቃዱን በማድረግ እድገት እያሳዩ መሄድን ነው የሚፈልግብን እንጂ በአንዴ ፍጹማን ካልሆናችሁ አይልም፡፡ ጻድቅ ሰው ማለት ፈጹም ሰው ማለት አይደለም፡፡

   **በመንፈስ ቅዱስ መመራት** (ሮሜ 8፡14፣ 26፣ ገላ 5፡16) የእግዚአብሔር ቃል ከሚናገረው ሌላ መንፈስ ቅዱስ የሚለውንም ሰምቶ ስራ ላይ ለማዋል መትጋት፡፡ እንደ አግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ቃሉ ለመኖርና በእግዚአብሔር ቤት ስራ በአገልግሎት ምንም ያህል የሚተጉ ቢሆንም እንኳ የራሳችን ጽድቅ እንዳለን አለመቁጠር፡፡ የምንደገፈው ክርስቶስ ኢየሱስ በሰራልን ስራና በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ ፍጹምነት በጎደለው ስራችን መሆን የለበትም፡፡

   **ለ/ ከሰዎች ጋር በሚኖር ግንኙነት፡ -** ከሰዎች ጋር መልካም በሆነ ኅብረት መገኘት። ከቤተሰብ አባላት፣ ከጎረቤት፣ ከስራ ባልደረቦች፣ ከጓደኞች፣ ከሥራ ኃላፊዎች፣ ከቤተ-ክርስቲያን መሪዎችና አባላት ጋር በሰላም መኖር። ከሰዎች ጋር ሕብረትን ሳያስተካክሉ ከእግዚአብሔር ጋር መወዳጀት አይቻልም።

እግዚአብሔር የእኛን ብዙ ኃጢአት ይቅር እንዳለን እኛም የበደሉንን ይቅር ማለት ይኖርብናል፡፡ ማር 11፡25-26፣

**ማቴ 7፡12፤** "ሌሎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው፤ ኦሪትም፣ ነቢያትም በዚህ ይጠቃለላሉና።"

**ማቴዎስ 6፡14-15፣** እናንተ የበደሏችሁን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ ደግሞ እናንተን ይቅር ይላችኋል። [15] ነገር ግን የሰዎችን ኀጢአት ይቅር የማትሉ ከሆነ፣ አባታችሁም ኀጢአታችሁን ይቅር አይልላችሁም።

**መዝ 21፡13፣** ሰው የድሆችን ጩኸት ለመስማት ጆሮውን ቢዘጋ እርሱም ይጮሃል (ሲጮህ) መልስ አያገኝም፡፡ ደግሞም ስጡ ይሰጣችኋል ስለሚል እግዚአብሔር በሰጠ ማንኛውም ነገር አቅም በፈቀደው መጠን የተቸገሩትን ለመርዳት ፈቃደኛ መሆን ይገባል፡፡

መስጠትን በተመለከተ ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የተገባው ጉዳይ የእግዚአብሔርን የወንጌል ሥራ ማለትም ለአገልጋዮች ቀለብና ለጸሎት ቤት ግንባታም ሆነ አያያዝ ለመደገፍ አቅም በፈቀደው መጠን ተሳታፊ መሆን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ተግባር መሆኑን ነው፡፡ ሐጌ 1፡2-11፣ ሚክ 3፡8-12

5. **ጽኑ እምነት፣** በእግዚአብሔር ማንነት ሁሉና የምንጸልይበት ጉዳይ እግዚአብሔር ሊያደርገው የሚችል መሆኑን ብቻ ሳይሆን የለመኑትን ለመሰስጠት ፈቃደኛ መሆኑን በእርግጠኝነት በማመን ጥርጣሬን በማስወገድ መጸለይ፣ ማቴ 9፡28-29፣ ያዕ 1፡5-7፣ ማር 11፡22-24፣

**በእምነት የምንጸልይባቸው መንገዶች/ሁኔታዎች፡**

**ሀ. የገጠመው ማንኛውም ዓይነት ችግር ወይም በሽታ እንዲያስወግድ ወደ እግዚአብሔር ልመናን በማቅረብ፡፡** የዚህ ዓይነቱ ጸሎት እጅግ የምናዘወትረው ነው፡፡

ምሳሌ፡- ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ጸሎት እንዲያስተምራቸው በጠየቁት ጊዜ ያስተማረው ጸሎት ዓይነት ማለት ነው፡፡

**ለ. የእምነት ማውጫ ዘዴዎችን በመጠቀም መጸለይ፡- (ስለዚህ የጸሎት ዘዴ "በእምነት መንካት" በሚል ርዕስ ከተዘጋጀው ትምህርት ማብራሪያውን መመልከት ይቻላል) ለምሳሌ ያህል፡-**

**ስዕለት በመሳል:-** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈረ የመጀመሪያው ስዕለት የተሳለ ሰው ያዕቆብ ነው፡፡ (ዘፍ 28፡20፤) ሀናም ልጅ ቢሰጣት መልሳ ለእግዚአብሔር እንደ ምትሰጥ ተሳለች፡፡ ስዕለት ሲሳሉ ግን እንከን ያለበት ወይም ጸያፍ የሆነ ነገር ለመስጠት መሳል ተገቢ አይደለም፡፡ የተሳሉትንም ነገር ቃልን ጠብቆ ለእግዚአብሔር ክብር ካልፈጸሙ ኃጢአት ነው፡፡ ሌዋ 22፡21፣ ዘዳ 23፡21-23፡፡

**ዘይት በመቀባት፡-** ያዕ 5፡14 የተጎዳው የሰውነት ክፍል ጥቂት ዘይት እየቀቡ በመጸለይ፡፡

**እጅ በመጫን/በእጅ በመዳሰስ፡- እንዲጸለይለት በተፈለገው ሰው ላይ እጅን በመጫን መጸለይ፡፡** ሉቃ 4፡40፣ ማቴ 8፡14-15

**የእምነት ቃል በመናገር መጸለይ፡** - ተራራውን በኢየሱስ ስም ተነቅለህ ወደ ባህር ተወርወር ማለት፤ ጌታ ኢየሱስ ያደርጋቸው የነበሩት ነገሮች እኛም ከእርሱ በማየት/በመማር እንድናደርጋቸው ነው፡፡ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፤ ጌታ ኢየሱስ በለሲቱን ያደረቀው፣ ሞቶ ተቀብሮ የነበረውን አላዓዘር ከሞት ያስነሳው የእምነት ቃል በመናገር ነበር፡፡ "ከእንግዲህ ፍሬ አይኑርብሽ"፣ "አልዓዛር ና ውጣ" የሚል የእምነት ቃል ተናግሯል፡፡ አንድ በክፉ መንፈስ የተያዘ ሰው ቢያጋጥም አጠገቡ በመቅረብ ለሰዓታት ቢቆሙ ክፉ መንፈሱ ሰውየውን ለቅቆት አይሄድም፡፡ በእምነት በጌታ ኢየሱስ ስም እንዲሄድ ቢያዙት ግን ይለቀዋል፡፡ ጌታ ኢየሱስ የተለያየ ችግር ለገጠማቸው ሰዎች ከችግራቸው ያድናቸው የነበረው የእምነት ቃል በመናገር ነበር እንጂ እግዚአብሔር አብ እንዲደርስላቸው በመጸለይ አልነበረም፡፡

**ሐ. ምሪት በመጠየቅ፡-** አንዳንድ ጊዜ የደረሰው ችግር እንዲወገድ ደጋግሞ ቢጸለይም መልስ ላይመጣ ይችላል፡፡ የገጠመው ችግር በተለያየ መንገድ ለማስወገድ ከመሯሯጥ በፊት ወይም የተለያየ ጥረት ቢያደርጉም ካልተወገደ የችግሩ መንስኤና መፍትሄ ምን እንደሆነ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት መጠየቅና በሚሰጠው ምሪት መሰረት መተግበር መልስ ያስገኛል፡፡ 1ሳሙ 30፡3-8፣ 2ሳሙ 21፡1-14፤

6. **በመጠበቅ መጸለይ**፡- በጸሎት የጠየቁት ነገር ሳያገኙ ቢዘገይም እየጸለዩ ጌታን በመጠበቅ በእምነት መጽናት ነው፤ እጅ ባለመስጠት/ተስፋ ባለመቁረጥ ጸሎት ማድረግ መቀጠልን የሚያመለክት ነው፡፡
   አንድ ጊዜ የጀመሩት ጸሎት ሳይመለስ ለቀናት ብቻ ሳይሆን ለዓመታት ሊቀጥል ይችላል፡፡ እግዚአብሔር እምነትን ሊመዝን ጸሎትን ሳይመልስ ቆየት ቢልም በፈቀደው ጊዜ መልስ መስጠቱ ስለ ማይቀር እየጸለዩ ጌታን መጠበቅ፣ ጸሎት ባይመለስም እንኳን ያልመለሰበት መንስኤ ስለሚያሳውቅ፣ መንስኤው ካወቁ ደግሞ የማስተካከያ እርምጃ ወስዶ በመጸለይ እግዚአብሔር እንዲሰማ ያስችላል፡፡
   አንዴ እግዚአብሔርን በጸሎትም ሆነ በአገልግሎት ትጋት መፈለግ ከጀመሩ በኋላ መልሶ በመተው፣ ከዚያም ቆየት ብሎ እንደገና መጀመር በፊት የተደረገው ጸሎት/ትጋት ስለ ማይታሰብ እንደገና እንደ አዲስ መጀመር ይሆናል፡፡ እግዚአብሔርን በመጠበቅ የሚጸለይ ጸሎት በየዕለቱ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራት እያከናወኑ እየጸለዩበት ላለው ጉዳይም በየዕለቱ የተወሰነ ጊዜ መድቦ በመጸይ መቀጠልን የሚያመለክት ነው፡፡ ሰውነት ቢደክምም በእምነት ባለመድክም የጀመሩትን ጸሎት ማካሄድ መቀጠልን የሚያሳይ ነው፡፡ ያዕ 5፡7-11፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዚህ ዓይነት ጸሎት ምሳሌ አብርሃም ከሳራ ልጅ ለመውለድ ለ25 ዓመታት በእምነት መጠበቁ ነው፡፡ ሮሜ 418–22፡፡ በሉቃስ 18፡1-5 ላይ ያለውም ሳይሰላቹ በጸሎት መቀጠልን የሚያመለክት ነው፡፡

   መዝ 40÷1 "እግዚአብሔርን ደጅ ጠናሁት (ጌታ እንዲረዳኝ በትዕግስት ተጠባበቅሁት)፤ እርሱም ዘንበል አለልኝ፤ ጩኸቴንም ሰማ።" (መዝ 37፡7)
   ኢሳ 64÷4 "ከጥንት ጀምሮ፣ በተስፋ ለሚጠባበቁት የሚደርስላቸው፣ እንደ አንተ ያለውን አምላክ ያየ ዓይን፣ ያደመጠ ጆሮ ፈጽሞ አልነበረም።"
   ሰቆ 3፡25-26፣ በእግዚአብሔር ተስፋ አይቆረጥም፣ ሰው የእግዚአብሔርን ማዳን ዝም ብሎ ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው፣

   **አጥብቆ መጸለይ፡- ያዕ 5፡17-18፤** አንዴ የጀመሩት ከጾም ጋር የተቀናጀ ጸሎት ከእግዚአብሔር መልስ ማግኘትን እስከሚታወቅ ድረስ ሳያቋርጡ ለሰዓታት፤ ለቀናት፣ ለሳምንታት ወይም ለወራት በመቀጠል የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የዚህ ዓይነት ጸሎት ምሳሌዎች ፡ - የነብዩ ኤልያስ በእስራኤል ዝናብ እንዲዘንብ የጸለየው 1ነገ 18:42-45፣ ንጉስ ሕዝቂያስ በታመመ ጊዜ የጸለየው 2ነገ 20:1-6፣ ጌታ ኢየሱስ በጌትሰማኔ የጸለየው ሉቃ 22:41-44፣ ቤተ-ክርስቲያን ለሐዋሪያው ጴጥሮስ የጸለየችው፣ ሐሥ 12:5፡፡
   አጥብቆ በመጸለይ ሂደት፣ ጸሎት በጀመሩበት ዕለት ከእግዚአብሔር መልስ ካልመጣ በሚቀጥሉት ተከታታይ ቀናት፣ ሳምንታት ወይም ወራት ወደ ሌላ ስራ ሳይኬድ በመሃል መሀል ሲደክም ጥቂት አረፍ እያሉ የጸሎት መልስ እስከ ሚመጣ ድረስ ተመልሰው መጸለይን የሚቀጥሉበት ነው፡፡

7. **የሚፈልጉት ነገር/ጉዳይ ግልጽ አድርጎ በመለየት መጠየቅ (አጠቃላይ ያልሆነ፣** Be specific)፡- ጉዳዩ ስለ ገንዘብ ከሆነ የሚፈለገው መጠን ምን ያህል መሆኑን መጥቀስ፣ የትዳር ጓደኛ ከሆነ፤ በጌታ ያመነ፣ የተማረ፣ የሚሰራው ሥራ ዓይነት፣ አጭር/ረጅም፣ ዘሩ ከየትኛው ብሔር እንደሆነ…ወዘተ፣ በመለየት እንጂ ጅምላ ነገር መሆን የለበትም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ከሆነ የትኛው ዓይነት ስጦታ የሚፈልጉ መሆኑን ለይቶ ማስታወቅ ይገባል፡፡ ሉቃ 18:35-42

8. **በኢየሱስ ስም መጸለይ፤** (ዮሐ 16፡23-24፤ 14፡13-14) ለምን በኢየሱስ መጸለይ አስፈለገ፡፡ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ፊት መቅረብ የምንችለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ብቻ ስለሆነ፣ የጽድቅ ስራችን እንደ መርገም ጨርቅ በመሆኑ እግዚአብሔርን ጠይቀን ለመቀበል ሕጋዊ መብት ስለሌለን፤ የጌታችን ኢየሱስ ስም ስልጣንና የተገባው የሚያደርገው የጽድቅ ሥራ ስላለው ነው፡፡ የእግዚአብሔር በረከት/ስጦታ ምንጩ የራሱ የእግዚአብሔር ብልጥግናና ልግስና ታላቅነት ሲሆን፣ መተላለፊያ መስመሩ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ 2ቆሮ 1፡20፤ ፊሊጵ 4፡19፣ ዕብ 10፡19-22፣ ኤፌ 2፡18፤

9. **ጸሎት አለመጸለይን ማስወገድ በረከት ከማግኘት ያርቃልና፡፡**ያዕ 4፡2-3፣ ሉቃ 15፡25-31፣ ዮሐ 4፡10፣15፡7 ለእግዚአብሔር ታዛዥ ቢሆኑም ካልጸለዩ እንደማይሰጥ ያሳያሉ፣ ማቴ 7፡7-8፣

10. **ለጸሎት ያነሳሳው ዋና ጉዳይ (ሞቲቭ) በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለው ማድረግ፡-** ያዕ 4፡ 2-3
የጸሎት መነሳሻ ጉዳይ ለግል ክብርና ጥቅም፣ የስልጣን ጥም ማርካት፣ ለማንኛውም ክፉ ዓላማ መሆን የለበትም፡፡ እግዚአብሔር አብ፣ በወልድ እንዲከብር ነው እንጂ፡፡ ዮሐ14፡13-14፣ 1ቆሮ 10፡31
የእግዚአብሔር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንድ አምላክ ታላቅ ማንነት እንዲታወቅና እንዲመለክ፡፡ የማያምኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ታላቅነት አውቀውና አምነው የጸጋው ተጠቃሚዎች በመሆን እግዚአብሔርንም እንዲያከብሩ፡፡ ያመኑትም ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር እንዲጠጉ፣ እርሱን በመምሰል እንዲያድጉ ሊሆን ይገባል፡፡ ኢያ 4፡24፤ ዘጸ 9፡15-16፣ 1ሳሙ 17፡45-46፣ 2ነገ 19፡19

11. **እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መጸለይ፡፡** 1ዮሐ 5፡14-15
የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ያልሆነውን ለማድረግ የተስፋ ቃል አይሰጥም፡፡ ስለዚህ ልንጸልይበት ስለፈለግነው ጉዳይ በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ውስጥ መኖሩን ፈልገን ማግኘት፡፡ በቃሉ ውስጥ ካለ ፈቃዱ መሆኑን እርግጠኛ ሆነን ወደ ጸሎታችን መግባት፡፡ 1ዜና 17፡23-24፣
ማር 14፡36፣ …ጌታ ኢየሱስ "ያንተ ፈቃድ እንጂ የኔ ፈቃድ አይሁን" እንዳለው በመከራ ውስጥ እያለፉ ቢሆኑም እንኳ ፈቃድን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት ተገቢ ነው፡፡ አንድ ክርስቲያን በሆነ ችግር ውስጥ እያለፈ ያለ ቢሆን፣ ጌታ ችግሩን እንዲያስወግድለት ከጸለየ በኋላ፣ ጌታ ሆይ ይህ ችግሬ አሁኑኑ እንዲወገድ ያንተ ጊዜ ባይሆን በዚህ ምክንያት እምነቴ ሳይደክም መጠበቅ እንድችል የሚያግዘኝ ጸጋ አብዛልኝ በማለት መጸለይ ይችላል፡፡

12. **ሁልጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ጌታን ማመስገንና በእርሱ ደስ መሰኘት፡-** እግዚአብሔር በጸሎት በፊቱ ያቀረቡትን ጉዳይ ወዲያው መልስ ሊሰጥ፤ ራሱ በወሰነው ጊዜ ለመፈጸም ጠብቁ ሊል ወይም አንዳንዱን ጥያቄ አይሆንም ሊል ይችላል፡፡ ስለዚህ እርሱ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ትክክልና ለጥቅማችን ስለሆነ፣ በጸሎት ያቀረቡት ጥያቄ ቢመለስም ባይመለስም በእግዚአብሔር ደስ መሰኘት ተገቢ ነው፡፡ በእርሱ ደስ ለመሰኘት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡ -
*ሀ.* የተለያዩ ምድራዊ ጉዳዮች እግዚአብሔርን ጠይቀውት ሲሰጥ ለጊዜው ደስ ያሰኝና ከአጭር ጊዜ በኋላ የሚረሳ ሲሆን የዘላቂ ደስታ ምንጭ ግን ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ፡፡
*ለ.* በክርስቶስ ኢየሱስ የማዳን ስራ የዘለዓለም ሕይወት ስለ ሰጠንና ያ ሕይወት የዘለዓለም ደስታ ሕይወት ስለሆነ፡፡ ዮሐ 16፡22፤
*ሐ.* በምድር ላይ ሳለን ደስታችንና በረከቶቻችንን ለመቀማት ከሚሰሩ ሰልፈኞች ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ሊያድነን ተስፋ ስለ ሰጠንና ከጎናችን ስላለን፡፡ ዮሐ 16፡33
*መ.* እግዚአብሔር እንዲሰጠን ከምንጠይቃቸው ምድራዊ በረከቶችም ሆነ የአገልግሎት የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ራሱ እግዚአብሔር ስለ ሚበልጥብን፡፡ መዝ 37፡4፣ በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ ፣ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል፡፡

13. **ጸሎት የሚጸለየው ወደ ማን ነው? ሀ) ወደ እግዚአብሔር አብ** ነው፡፡ ማቴ 6፥9 “እናንተ ግን እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ፤ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ፤…”
**ለ) ወደ ጌታ ኢየሱስ ክስቶስ ነው፡** - ዮሐንስ 14፡13-14፣ አብ በወልድ እንዲከብር፣ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፤ [14] ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ፣ እኔ አደርገዋለሁ። መለኮታዊ ማንነት ወደ ሌለው ወደ ማንኛውም ፍጥረት ጸልዩ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም፡፡
አይቶ የሚራራና ሰምቶ የሚመልሰው አምላካችን ወደ እርሱ እንድንጸልይ ዕድል ስለሰጠን ምስጋና ለስሙ የሁን!!!

© ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ. ም.